# ብአዴን እና ሰዉ መሆን

====================

ሽንቁጥ አየለ

ሰዉ የሆነ ፖለቲከኛ በትንሹ ቢያንስ አንድ ቀን ሶስት ነገር እራሱን ይጠይቃል :-

1ኛ-የምሰራዉ ስራ ልክ ነዉ?

2ኛ -አጠገቤ ያሉ አለቆቼ የሚሰሩት ስራ ልክ ነዉ?

3ኛ-ህዝባችን ከእኔ ስራ እና ከአለቆቼ ስራ እየተጠቀመ ነዉ?

ሆኖም ብአዴን ዉስጥ ያሉ ፖለቲከኞች እንኳን ሶስቱን ጥያቄ አንዱንም ጥያቄ አይጠይቁም። ጠይቀዉም አያዉቁም። መጠየቅም አይፈልጉም።

እነሱ የሚጠይቁት አንድ ነገር ብቻ ነዉ። "እንዴት ሆዴን መሙላት እችላለሁ? አለቆቼ ተበሳጭተዉ ከስራ እንዳያባርሩኝ እና ሆዴ እንዳይጎድል አለቆቼን እንዴት ማስደሰት እችላለሁ?"" በቃ። ይሄዉ ነዉ። ብአዴን ከሆንክ ከዚህ በላይ አትሄድም።

ሚሊዮን አማሮች ከምድረ ገጽ ተደመሰሱ ብትባል: አማራ ላይ የዘር ማጥፋት ሲጧጧፍ ብታይ ምንም የሚያስጨንቅህ ህሊና የለህም።ለምን ብለህ ለመጠየቅም ወኔ የለህም። ብአዴን ከሆንክ ሆድህ እስካልጎደለ ድረስ ሁሉም ነገር ትክክል ሆኖ ነዉ የሚታይህ።

ስለሆነም ብአዴን እና ሰዉ መሆን የሚለያዩት አንድ ሰዉ ገና የብአዴን ፎርም ሲሞላ ነዉ።

ከአራት እና ከሶስት አመት በፊት እንዲህ ሆነ። በሽ የሚቆጠሩ ከጉራ ፋርዳ የተባረሩ አማሮች አዲስ አበባ ዉስጥ በየ መንገዱ ስለተበተኑ ጥቂት ነገር እንዲረዱ አንድ የርዳታ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም አዘጋጅተን መንቀሳቀስ ጀመርን። ከዚያም ብአዴኖች እንቅስቃሴአችንን ከፖለቲካ ጋር አገናኙት። ከፖለቲካ ጋር ግንኙነት እንደሌለዉ አጥብቀን ገለጽን። እኛን ለማስፈራራት ሞከሩ። ሆኖም እኛ እርዳታ ማሰባሰቡን ማቆም አልቻልንም። ወገን እየጠፋ ሌላ ማድረግ ባንችል ባለን አቅም መርዳት እንዳለብን ስለወሰንን ሰዎቹን ለመርዳት ሙከራ ማድረጋችችንን ቀጠልን። በክርስቶስ ስም እዉነቱን ለመናገር እንቅስቃሴአችን ከፖለቲካ ጋር ምንም ግንኙነት አልነበረዉም።

ከዚያ ብኋላ ብአዴኖች ምን ቢያደርጉ ጥሩ ነዉ? ከቤቱ ተፈናቅሎ በጎዳና የተበተነዉን ህዝብ ማስፈራራት እና መዋሸት ጀመሩ። "ነግረናችኋል እርዳታ ከነዚህ ሰዎች እንዳትቀበሉ። እነሱ ተቃዋሚዎች ናቸዉ። መንግስት ከተቃዋሚ እርዳታ የተቀበለን ሰዉ መልሶ አያሰፍርም። አይረዳም: እኛ አሁን እናሰፍራችኋለን። መንግስት ይረዳችኋል ። መንግስት ግን የሚረዳችሁ ከነዚህ ሰዎች /ከተቃዋሚዎች/ እርዳታ ካልተቀበላችሁ ነዉ።" እያሉ ማስፈራራት ጀመሩ።

እናም እንዲህ አድርገዉ ዋሽተዉ ሲያበቁ ተፈናቃዮቹን እንኳን ሊረዷቸዉ ሚኒሻሻ የሚባል እጅግ ሩቅና ጫካ የሆነ ወረዳ ዉስጥ ወስደዉ በተኗቸዉ። እንዲረቡ። እንዲሞቱ። ወባ እንዲጨርሳቸዉ።በዚህ ወረዳ ዉስጥ እንኳን ምግብ ሊኖር የበሰበሰ በቆሎ እንኳን አልነበረም። እናም ብዙዎቹ በረሃብ ሞቱ። ህጻናት ወዲያዉ በወባ ሞቱ። አንዳንድ ጉልበት ያላቸዉ ሰዎች እየጠፉ ከወረዳዉ አመለጡ። በጣም የሚዘገንነዉ ደግሞ ከሚኒሻሻ ወረዳ ሰዎቹ እንዳያመልጡ ጠባቂ ሆነዉ የተመደቡት ብአዴኖች ነበሩ። ከወረዳዉ ጠፍተዉ የመጡት ሰዎች እንዳብራሩልን ሊያመልጡ ሲሞክሩ በጥይት የተገደሉ ሰዎችም ሞልተዋል። ይሄንንም የፈጸሙት ብአዴኖች ናቸዉ።

ይሄ ሁሉ የሚደረገዉ ከሰዉነት ተጠይቅ በተጣሉት ብአዴኖች ነዉ። አማራ ላይ የዘር ማጥፋት ሲከናወን በፊታዉራሪነት የሚመራዉ ብአዴን የሚባለዉ አማራን እወክላለሁ የሚል ድርጅት ነዉ።

ብአዴን እና ሰዉ መሆን መቼም ተገናኝተዉ አያዉቁም። አሁን ደግሞ ህዝቡ በረሃብ እያለቀ እነሱ ይጨፍራሉ። ሳያፍሩ ዉስኪ ይጠጣሉ። ሳይፍሩ ስለ እድገት ይናገራሉ። ብዙ ሚሊዮን ብሮችን ለምናምንቴ ድግስ ያባክናሉ።

እንዲህ አይነት ምንም ህሊና እና ወኔ የሌላቸዉ ፍጡራን እንዴት ተጠራርተዉ ሊሰባሰቡ እንደቻሉ አስገራሚ ነዉ።ወይም ደግሞ ህዉሃት በምን ጥበብ እንዲህ አይነት እምነተቢስ ሰዎችን በባትሪ ፈልጋ እንዳገኘቻቸዉ ያስደንቃል። ህሊናና ወኔ ያለዉ ሰዉ እነዚህ ሰዎች መሃል ቢገባ በሶስተኛዉ ቀን ወይ ጨርቁን ጥሎ ይሄዳል ወይም ደግሞ አንድ አምስት አለቆቹን ገሎ እራሱን ያጠፋል።

ፕሮፌሰር ሰባስኪ የተባለዉ የጣሊያን ታሪክ ጸሀፊ ስለኢትዮጵያ ታሪክ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል- " ከሀበሻ ማህበረሰብ ዉስጥ ሁለት ጽንፈኛ ባህሪያት አሉ። ይሄዉም ፍጹም የሆነዉን ጀግናም ሆነ ፍጹም የሆነዉን አድርባይም የምታገኘዉ ከሀበሻ ነዉ።"

እዉነት ነዉ ሀበሻን በትክክል ገልጾታል። ወይ ፍጹም ጀግና ወይም ፍጹም አድርባይ ባህሪያት በደንብ ያሉበት ማህበረሰብ ነዉ።

ሰዉ ፍጹም አድርባይ ሲሆን ከሰዉነት ተጠይቅ ይወጣል። ብአዴኖች ማለትም ይሄዉ ናቸዉ። ሰዉነትና ብአዴን ተገናኝተዉ አያዉቁም።እንደሰዉ እራሳቸዉን ሆነዉ ለመቆም ብቃቱም: ወኔዉም ;: ህሊናዉም የላቸዉም። ሆዳቸዉ ህሊናቸዉና ወኔአቸዉ ላይ ቆሞበታልና። እንዲህ ሲሆን ሰዉ ከሰዉነቱ ይነጠላል።